# ስለ የትምህርት ጥራት ብናወራስ?

ከሚገርሙኝ ነገሮች አንዱ የትምህርት ጥራት ነቃፊዎች ብቃትና ፡ ጥራትን ከምን ጋር አወዳድረው፡ እንዴት መዝነውት፡ እንደሚናገሩ ነው፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከማንም የተሻለ እውቀትና ልምድ እያላቸው ፡ ጀሮ ዳባ ልበስ በማለት መናገር አለመቻላቸው ፡ አንዳንዱ ጽንፈኛ ተቃዋሚ ይሆንና አይንህን በጨው ታጠብ በሚል አይነት ምንም እንደማታውቅ ሲቀድልህ ስለሚገርም፡ አንዳንዱ ደግሞ ጭልጥ ያለ ደጋፊ ይሆንና ጨረቃ ላይ የደርስን ያስመስለዋል፡ ጭፍን ደጋፊዎች ግን ይሻላሉ፡ ስህተት ቢሆንም ንግግራቸው ሞራል ሰጪ ነው። ግን ስህተት ነው። ከንደነዚህ አይነት ገጠመኞችና፡ አንዳንድ በልጅነትና ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ያስተማሩኝ አስተማሪዎች ትውስታዎችን ላጫውታቹ ስለፈለግኩኝ ነው።

የትምህርት ጥራት በሚመለከት የተደገው ውይይት፡ ጥራት ለመጠበቅ እየተደረግ ያለው ጥረትም ትክክል ነው የሚያስብል ስለሆነ ነው ጽሁፉን ያዘጋጀሁት።

ይህ ጽሁፍ በአብላጫው የግሌ ትዝብት ነው የብቻየ ይሁን እንጂ ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ከወስኔ በፊት የተለያዩ ጏደኞቼ በጉዳዩ ፡ ውስን የሆነ ጥናት እንድናደርግ በሃሳቤ እንዲተባበሩ እና፡  አንዳንድ የቤት ስራዎችን እንድንሰራ ተግባብተን ፡ የየራሳችንን የቤት ስራ ሰርተን በመጨረሻ ላይ 99% የተግባንበት ጉዳይ ሲሆን እኔ በፅሁፍ ለማቅረብ የወሰንኩት፡ ትምህርት ጥራት በሚመለከት ውይይት በማዳመጤና፡ በተለያየ ጊዜ ይህንን የሚመለከት ክርክሮች ያጋጥሙ ስለነበሩ ነው። እና ይህው በረከቱ እላለሁ፡፡

በመጀመርያ፡ይህን ፅሁፍ አሁን በመምራት ያለው የፖለቲካ ድርጅት እጹብ ድንቅ መተክያ የሌለው፡ በእግዜብሄር የተሾመ ድርጅት ነው በማለት ለውደሳ የቀረበ አይደለም፡ ያልተሰራውም ተሰራ ብሎ ለማውራት አይደለም፡ ይህንን ፅሁፍ ማንም ስፖንሰር ያላደረገው የግል ግንዛቤ የሚያንጸባርቅ ብቻ ነው። ስህተት ሊኖረውም ይችላል፡ ምክንያታዊ እና በእውቀት የተመሰረተ እርምት ካለ ተቀባይነት አለው። በተለይም ደግሞ የአገር ጉዳይ ስለሆነ ፡ በሬ ወለድ ንግግር ሳይሆን ፡ በጭብጥ የተመሰረተ ክርክር ቢደረግ ሊጠቅም ይችላል በሚል፡ አንባቢዎች ለማሳተፍ ነው። እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በረባ ባልረባ መደናቀፍ የለባቸውም የሚል እምነትም ስላለኝ ነው። ምክንያታዊ የሆነ መሻሻል መጠቆም ተገቢ ስለሆነ። መሻሻል የሚገባውም እንዲሻሻል በግሌ የሚገባኝ ለመጠቆምም እሞክራለሁ፡፡

ተማሪዎች እያለን ትዝ የሚሉኝ የሚገርሙና የሚያስቁ ገጠመኞችም ለጨዋታ ያህል ለማካፈል ስለፈልግኩኝ ነው። ለፅሁፉም ጠቃሚነት ስላላቸው ነው።

ከማስታውሳቸው አንዱ፡ የሂሳብ ትምህርታችን ላይ √2 ኢራሽናል ነው እና አረጋግጥ የሚለው ነው፡ (ፕሩፍ ጥያቄ ነው)፡ ይህ ጥያቄ በጣም ጊዜ ይወስዳል ለመገንዘብ፡ በተለይ እንግሊዘኛ ሁለተኛ ቋንቋዋ ለሆነ ሰው፡ ይባስ ብሎ አስተማሪህ ጋርም የምትግባባው

በሌላ ልጅ ሆነህ ብዙም በማታውቀው ቋዋንቋዋ ነው፡ ትምክሕተኛ የሆነ አስተማሪ ከሆነ ደግሞ የባሰ ነው፡ ሰድብ ነበረ የሚከተለው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የአንዳንዶቹ የነበሩት አስተማሪዎች ብቃት አሁን ትልቅ ሰው ሆነን ሳገናዝበው፡ እህድግለነ ያስብላል፡፡

ይህንን √2 ኢራሽናል ነው የሚለውን ጥያቄ ይኸ በግዜው ለነበረው አስተማሪ በደንብ እንዲያሰረዳኝ በትርፍ ሰአት ላይ ጠየቁት እና ያኔ ሊያሰረዳኝ ሞከረ ግን አልቻለም፡ አስተማሪው ይወደኝ ነበር ፡ ጥሩ ሰው ነገር ነበር የነበረው፡ በመጨረሻ ግን የሂሳብ ህግ ነው ዝም ብለህ ተቀበለው ነበር ያለኝ፡ የኦርጋኒክ ኬሚስትሪ  በጣም የምወደው ትምህርት ነበርና የፎርሙላው ርዝመት ለምን እናሳጥረውም አልኩት ፡ አስተማሪው ጥያቄውን ስጠይቀው፡ የቂጣው ናዳ ትዝ ይለኛል፡ እንዴት ቢለኝ ግን የራሴ የጥናት መላ ስለነበረኝ ምናልባት ሊጠቅም ይችል ይሆን ነበር፡ በሌላ ጊዜም ይህንኑ አስተማሪየ ይህ ሁሉ የኦርጋኒክ ኬሚስትሪ ትምህርት ምን ይጠቅማል ብየ በእረፍት ሰአት ጠይቄው፡ ዝምብለህ እጥናው የሚል ነበር መልሱ። ቀላሉ መልስ ግን፡ የለበስከው ልብስ፡ የምትበላው ምግብ፡ ስትታመም፡ የምተጠጣው ውሃ ሁሉ ኬሚስትሪ ነው፡ ማለት የተሻለ መልስ ይመስለኛል። ሌላው የፊዝክስ አስተማሪ ስለ ድምፅ ሞገድ ሲያስተምር ፡ “ላምዳ” ስለሚባለውን የግሪክ ፊደል ፡ ጥያቄ ይዠለት ሂጀ የግሪክ ፊደል መሆኑ ነገርኝ፡ ሆኖም ግን ድምጽን ለመግለፅ ስለሆነ ለምን ፡ የራስችን ፊደል አንፈጥርለትም ብየው፡ ላምዳ ከምንል ፡ “ድ”፡ ብንለው ይቀላል ስለው፡ አያትህ የፈለሰፉት መሰለህ እንዴ የሚል ሞራል የሚሰብር መልስ ነበር የሰጠኝ።

ከሁሉም አስከአሁን የማስታውሰው በጣም ደደብ እና ተሳዳቢ መምህር ነበረን፡ አማርኛ አስተማሪ ነበር። አማርኛ በጣም ጥሩ ቋዋንቋዋ ነው፡ የማንም ሰውም አየደልም፡ አማርኛን ግን የግሉ አድርጎ ነበር የሚስበውያ አስተማሪ፡ ትግርኛ ስታወራ ከሰማህ ፡ ሂድ ከዚህ ይህ የወፍ ቋዋንቋዋህን ይዘህ ነበር የሚለው፡ እሱ ስላለማይገባው የወረደ የትምክሕተኞች አነጋገር ነው አነጋገሩ ሁሉ፡ የቋዋንቋዋ ሰው ቢሆን ኖሮ አማርኛን ትግርኛ ተናጋሪን ለማስተማር ቀላሉ  ትግርኛን ማወቅ ወይም መረዳት መቻል ነው ፡ ኦሮሞ ተናጋሪን ልታስተምረው ከፈለግክም ኦሮምኛውን ብታወቅ በቀላሉ ታስረዳዋለ፡ ስራህም ማስተማር ስለሆነ፡ የቋዋንቋዋ ሰው ከሆንክ ችሎታ ሊኖርህም ይገባል። ግን የቋዋንቋዋ ሰው አልነበረምና ስድብ ብቻ ነው።  የደርግ ካድሬ የነበረ ሊሆን እንድሚችልም እገምታለሁ፡ በቃ ቆሻሻ ሰው በሚል መደምደም ይቻላል፡፡

ዩኒቨርሲት እያለን ደግሞ የዩኒቨርስቲ የአፈር ሳይንስ አስተማሪ የነበረው አስተማሪ ላውጋቹ፡ ክፍል ውስጥ ስለ አፈርና ሳይንስ ፡ ከሚያስተምረው በተያያዥነት የጎምን ዘር እንደ ምሳሌ ጠቀሰ ፡ በወቅቱ በእጀ ላይ የነበረው ኒውስ ዊክ መፅሄት ውስጥ ስለ (ሬፕ ሲድ) የጎመን ዘር የሚጨመቅ ዘይት የሚያወራ ነበርና ትዝ ሲለኝ ገለጥ አደረግኩት፡ ኒውስ ዊኩን ስገልጠው አይቶ ተናደደ  እና ከክፍል አስወጣኝ ፡ የኢምፐሪያሊስቶች መፅሄት መሆኑ አስጠልቶት ነው መሰለኝ። እስከአሁን የሚገርመኝ ምንድነው የምታየው ብሎ እንኩዋን እልጠየቀም፡፡ ያሰው ታድያ በአሁኑ ዘመን ደግሞ ዋና የኢሀደግ ደጋፊ ነው፡ በዩናይትድ ኔሽን  ባለስልጣን መሆን በቅቷል። ሳየው ሁሌም ይገርመኛል።

ሚዛኑ ለመጠበቅ ያህል፡ እነዚህ አስተማሪዎች እነሱን ካስተማሩዋቸው የወረሱት ወይም ጊዜው የሚጠይቀው ስለሆነ ሊሆን ይችላል እንጂ መጥፎ ሰዎች ናቸው ለማለት አይደለም፡ የነበሩት አጋጣሚዎች ለመጨዋወት ያህል ነው፡ አስተማሪዎቹን ለማንቋሸሽም አየድለም። እነኝህ አጋጣሚዎች ለፅሁፉ ማጣፈጫ እንጂ ሌላ አላማ የለውም። በጣም አዋቂ አስተማሪዎች፡ ታታሪ የምርምር ሰዎችም የነበሩ እንደነበር መታወቅ አለበት፡ ከቤተሰብ ቀጥሎ ፡ በጣም የሚወደዱ እና የሚከበሩ አስተማሪዎች ነው።

ከኢትዮጵያ ከመውታቴም በፊት አገር ቤት ውስጥ፡ ውጭ አገር ስኖርም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሲወራ ስለ አሁን ያለው የትምህርት ጥራት ሰዎች ሲያወሩ ፡ ቴክኒካል እውቀት ያላቸው በሚያስመስሉ ቃላቶች በመጠቀም ሲከራከሩ፡ ጮኸው በንዴት ሲናገሩ አጋጥሞኛል በተለይ እዚሁ በውጪው አለም፡ በየቀኑ የሚያጋጥም ነገር ነው፡ አንዳንዶቹ በቃ በምእራቡ አለም በመኖራቸው ብቻ፡ የማንኛውውም እውቀት ባለቤት የሆኑ ይመስላሉ ሲናገሩ ፡ የንዴት እስክስታ እየመቱ ሲስዘባርቁ ብዙ ጊዜ አጋጠሙኝ፡ አንዳዶቹ ደግሞ እውቀቱ አላቸው ግን፡ ፖለቲካዊ አላማቸው በግርግር የሚሳካ እየመሰላቸው ነው መሰለኝ ነገሩን ያራግቡታል።

የትምህርት ጉዳይ፡ ሲነሳ ሁሌም የማቀርባቸው ጥያቄዎች አሉ? ጥያቄ የማቀርበው ለሁለት ነገር ነው።

1. ብዙ የማላውቀው ጉዳይ ስላለ ለማወቅ
2. ተናጋሪው የትምህርት ጥራትን የመመዘን ብቃት እንዳለው ለማወቅ ነው።

ጥያቄውም፡ አሁን ያለው ትምህርት ጥራት ያለው ስለመሆኑና አለመሆኑ እንዴት አወቅክ? ምን ጥናት አደረግክ? የትኛው የተጠና ጽሁፍ አነብበክ? አሁን ያለው ትምህርት ከምን ጋር አወዳድረህ ነው ? የመሳሰሉት እና እነዚህ ጥያቄዎች ሲነሱ ። አንዳንዶቹ እንደ አንዝርት ሲስከረከሩ ወይም ሲስዘላብዱ አየን ማለት ነው።

የአንዳንዶቹ የሚገርም ደግሞ፡ በዘመነ እንጦንጠንዮስ ለማ በገበያ የጻፋትን ሰማይ ላይ ከበው፡ ስለ ኒኩሌየር ኢንጂነሪንግ ከሚያሰላስሉት አዳዲስ ምሁራን ጋር ፡ ሆኖም ግን እነሱ የማይወዷቸው ስለሆኑ ብቻ ሲያብጠለጥሉዋቸው ፡ ሲያወዳድሩ ሳይ ይገርመኛል።

አንድ በጣም የሚያሰቀው ደግሞ አንድሰውየ አሉ፡ የድሮ መዝገብ ቤት ሰራተኛ ነበሩ ይባላል ፡ በሳቸው አባባል “አገሪትዋ ኢህዴግ በሚባል ጭራቅ መንግስት በመተዳደርዋ፡ አዘቅት ላይ ገብታ አለቀላት አይነት ነው ንግግራቸው ሁሉ” በጣም ይቃወማሉ፡ “የትግሬ መንግስት ነው የሚሉት፡ ትግሬዎች ለማስተዳደር እና አገር ለመራት አይሆኑም ይሉና፡ ትግሬዎች ወታደርነት ነው ጉብዝናቸው ይላሉ፡ ተገልብጠው ደግሞ ትግሬ ብቻ እኮ ሆነ ወታደሩ ይላሉ ” ብቻ በሳቸው ስሌት እያንዳንዱ ዘር የስራ ምድብ አለው። መብታቸውም ነው መዘላበድ ፡ ኢንጂነር ነኝ የነበርኩት ነው የሚሉት ደግሞ። ስለ ትምህርት ጥራት፡ ስለ ማስተዳደር እያወሩ ፡ የንዴት አስክስታ ሲመቱ ያስቃል “ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ እንደሚባል አይነት ነው፡፡” በጣም ዘረኛ ናቸው።

ያለመማራቸው ሲጠቀስ ፡ ያልተማረ ጥሩ ሃሳብ ሊያመጣ አይችልም ለማለት አይደለም፡ የተማረም ያልተማረም በትምህርት ፖሊሲ እና ጥራት ሊተች የሚችል ይመስለኛል፡ ጥሩ ትችትም ሊያቀርብ ይችላል፡ ነገራቸው ሁሉ ውሸት ስለሆነ ማዳመጥ ስለሚሰለች እና አንዳንድ የዳያስፖራው  ተራኪዎችን የሚወክል ባህሪ ስለሆነ ለመዝናናት ያህል በፅሁፉ ጣል ለማድረግ ፈልጌ ነው።

በነገራችን ላይ። ትምህርት የሌላቸው ግን በንሮ ልምድ የተካኑ የኑሮ ጠበብት ፡ በጣም ብዙ ገበሬዎች፡ ነጋዴዎች፡ የቤት እመቤት እናቶችን በእያንዳዳችን ሂወት ውስጥ ስላጋጠሙን፡ ማክበርና ማስታወስም ይገባል። ትምህርት ብቻውንም ምንም ማለት እንዳልሆነም ከአንዳንድ ዋጋ ቢስ ሰዎች ብዙ አይተናልና።

መመራመር እና ሃቅን የሚወድ ለሚሰማው ነግር ሁሉ በደንብ ለማጤን ጊዜ ይሰጣል፡ የሚነገርው፡ ይሚተቸው 1% እወነታ ይኖረው ይሆናል በማለት የራስን የቤት ስራ መስራት ጥሩ ባህል ነው። በዚህ አስተሳሰብ ፡ እኔና ጏደኞቼ አስኪ ቀለል ያለ ጥናት እናድርግ ተባብለን ተስማማን ፡ በትምህርት ዙርያ ላይ ጽሁፎችን ስናነብ ብዙ ጊዜ ቆየን፡ አሁን በቅርብ ጊዜ በ 2011 እና በ 2012፡ አንዱ ጏደኛየም 2013 አገር ቤት ጎራ ብቅ ብለን ነበር፡ እዚህ ስማቸው ሊገለፅ የማይፈልጉት ጏደኞቼም እኔም የመሰለንን የየራሳችን ጥናት አንድናደርግ በተስማማነው አደረግን የተለያዩ መረጃዎችን አሰባስበን ተወያየን፡፡ የወያኔ በመባል የሚወቀሰው ሲቪል ሰርቪስ ሳይቀር የትምህርት ቤቱ አስተማሪዎችን ፡ አንዳንድ የከሪከረለሙ ይዘት፡ አንዳንድ ተማሪዎችን አንደበታቸው ለመረዳት ሞከርን፡ በአንደኛ ደረጃ፡ ሁለተኛ ደርጃ እና ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችንም ጠይቀናል፡ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ስጠይቃቸው የነበሩ ጥያኤዎችን እንደ ማዝናኛ በመጠቀም የማቃቸው ተማሪዎች ለአስተማሪዎች እንዲጠይቁ  በማድረግ ሞከርን።

እኔና ጏደኞቼ የደረስንበት አጠቃላይ መደምደምያ፡ በአገር ደረጃ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች፡ ይዘት፡ እና ጥልቀት ለውጥ እንዳለ እና የተሻሻለ ነው። አስተማሪዎች ለጥያቄዎች ያላቸው ክብር የተሻለ ነው። ንፅፅሩ ያደረግነው ከበፊት ከነበሩ የትምህርት አሰጣጦች እንጂ ከማንኛውም አለም ያለ የትምህርት ጥራትን ይዘት አይደለም፡ ይህንን ያደረግነው የምናውቀውን ያህል ለማድረግ ብቻ  ነው፡ የተሟላ ጥናት አንዳልሆነም ተግባብተንበታል። ከዚህ በተጭማሪ በይዘትና የትምህርት አሰጣጥ የተሻሻለ ቢሆንም፡ ከትምህርት ቤት ወደ ትምህርት ቤት፡ ከክልል ወደ ክልል፡ ከግል እና መንግስት ትምህርት ቤቶች ልዩነት ሊኖር እንደሚችል ገምተናል። የአስተማሪዎች ብቃትም ሊዩነት አለ።

ከሌሎች አገሮች የትምህርት ጥራትና ፡ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ማወዳደር ራሱ የቻለ ከባድና ውስብስብ የጥናት ስራ ለባለሞያዎች የሚተው ጉዳይ ነው ብለን ስላሰብን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ፡ የጏደኞቼ ሃሳብ ባይሆንም በአገራችን የትምህርት ሂደት እና አሰጣጥ አንድ መሰረታዊና ትልቅ ችግር ያለ መሆኑ ለመጥቀስ እፈልጋለሁ፡ ይህ ችግር ስር የሰደደ እና በአገራችን ለረዥም ጊዜ የቆየ ችግር ነው፡ በቀላሉ ለመፍታት ብዙ ስራን የአሚጠይቅ

ጉድይ ይመስለኛል። እስከ አሁን ብዙም ሊቀረፍ ያልቻለው  አሁንም ድሮም የአገራችችን ትምህርት ቲዮሪ ላይ በጣም ያተኩራል። ስለሆነም የአገራችን ምሁር በአብዛኛው፡ የወረቀት ነብር ነው የሚሆነው። አሁንም ችግሩ አለ፡ ድሮም ነበረ፡ በወሳኝ መልኩ ሊፈታ ግን ይገበዋል።

ስለሆነም እንደሚመስለኝ የአገራችን የትምህርት ፖሊሲ አንጻለ ሆኖ፡ የትምህርት ፕሮግራሞች ግን ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ተደርገው መቅረብ መቻል አለባቸው፡ ተማሪዎች፡ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ሊያገጥማቸው የሚችል የግል፡የማህበረስብ እና በአለም ደረጃ ያሉ ችግሮችን  እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ ለመገንዘብና ሃሳብ እና ልምድ ለመቀያየር መሆን መቻል አለበት፡ መጋቢና ተመጋቢ ግንኙነት መሆን የለበትም በተማሪና አስተማሪዎች ያለው የትምህርት ሂደት ግንኙነት፡ የቲዮርይ ትምህርት ውይይት በሚያስነሳ ፡ ተጨባጭና ችግር ፈቺ በሚሆን መልክ መሰጠት መቻል አለበት፡ እያንዳንዱ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገትም ችግር ከመፍታት ተያይዞ ያደገ እንጂ ፡ ዝምብሎ ከሰማይ የወረደ ስላልሆነ ነው፡ ችግር እናንሳ ከተባለ ደግሞ በሺ የሚቆጠር ችግርም መዘረዘር ይቻላል፡ ትምህርት ቤቶች ይህንን ማድረግም ይችላሉ ማድረግም አለባቸው። እንዲህ ከሆነ ትምህርት ቤት ጣፋጭ፡ ጠቃሚ፡ የማይሰለች ይሆንና፡ ለወደፊቱም የአገሪቱ ተስፋ የበለጠ ብሩህ ያደርገዋል። ስለሆነም ችግር ፈቺ ተኮር ትምህርት መሆን ይገባዋል።

ሁለተኛ እና ዋናው የዚህ ፅሁፍ አላማ ለመሰንዘር የፈለግኩት እንደሚከተለው ነው፡ ከተቻለ፡ የኢትዮጵያ ቴለኢዚኸሮን እና የውጪው አለም ኤምባሲዎች ጋር በመተባበር፡ ከየአገሩ ወክለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከሆኑት የተወለዱትን ልጆች ወይም ውጪ ከሚኖሩት ትውለደ ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች፡ ከየክልሉ ከሚውጣጡ አገር በቀል ተማሪዎችን፡ እነሱም፡ በአንደኛ ደረጃ፡ ሁለተኛ ደረጃ እና ዩኒቨርሲቲ  ተማሪዎችን የሳይንስ እውቀት ውድድር እንዲደረግ ነው ሃሳብ ለማቅረብ ነው የፈልግኩት፡፡ በውድድሩ የሳይንስ እውቀት በወሳኝነት፡ የአንግሊዘኛ ቁዋንቁዋ ደግሞ ሰዋስውን እንጂ ፡ የመናገር ቅልታፌና ፡ የአነባበብ ቅላጼ (አክሰንት) መሆን የለበትም ።

የዚህ ውድድር ጥቅም፡ እነኝህ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይነት ካለው ቤተሰብ ያደጉ፡ የሚማሩት ግን በተለያየ አለም ነው፡ ለውድድር ተቀራራቢ አቅም ነው ያላቸው፡ ምናልባት በምእራባውያን ወላጆች ቤተሰብ ያደገ ልጅ ፡ ከትምህርት ቤት ከሚያገኘው ሳይንሳዊ እውቀት በተጨማሪ ቤተሰብ እና በአብዛኛው ማህበረሰባ ላይ ስለሚያገኘው ውድድሩ ትንሽ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡ ሁለቱም ግን በተመሳሳይ ቤተሰብ ግን በተለያየ አለም ያደጉት ስለሆነ ማወዳደር ይቻላል ፡ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ፍንጭ ስጪ ጭብጦች ለተማራማሪዎችና ፖሊሲ አቅጣጫ ቀማሪውች ሊያስገኝ ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከዚያም በላይ በዚህ ሁለት አለም የሚኖሩ ወንድማማች ሕጻናት፡ ታዳጊዎች እና ጎረምሶች ያቀራርባል። ጥሩ ማዝናኛም ነው።

በዚህ ውድድር ፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያሸንፋሉ በሚል $100 አሸገቬአላሁ። በዚሁ ጽሁፍ የተስማማቹ በፈለጋቹት ጎራ ተሰልፋቹ $100 አስይዙ እና በመጨረሻ፡ አሸናፊዉም

ተሸናፊውም ያዋጡትን ብር ተሰብስቦ፡ የትምህርት እድል ላላገኙት ህፃናት ማገገ፡ ወይም እሸናፊ ለሆነው ትምህርት በይበልጥ ማሻሻያ ሊውል ይችላል።

ለማንበብዎ እናመሰግናለን

ሙሉብርሃን ዳኘው

09/02/14